የእንሰት አምራች ገበሬዎች አሠራር ዘይቤን በመከተል በባዶ መሬት ላይ በአጭር ጊዜ እንሰትን ማልማት ይቻላል:: አምቾ ከተቀበረ በዘጠኝ ወር (ጥቅምት/2004) እነዚህ የእንሰት ችግኞች በቁመት እስከ አራት ሜትር አድገዋል::



በቅርብ የሚገኝ የከብት ፍግና በቂ እንክብካቤ አግኝተዉ በዝናብ ዉሃ ብቻ ያደጉ ናቸዉ::



ከአንድ አምቾ የተገኘ የችግኝ ብዛት በቁጥር (የ6 ዝርያዎች አማካይ) :- ሙሉ አምቾን በመቅበር በአማካይ 26 ችግኞች፤



አምቾ ለሁለት ተሰንጥቆ ከተቀበሩት በአማካይ 65 ችግኞች፤



አምቾ ለአራት ተሰንጥቆ ከተቀበሩት በአማካይ 80 ችግኞች ተገኙ::

የስዊድን ምርምር ካዉንስል ለጥናቱ የገንዘብ ድጋፍና የአረካ ግብርና ምርምር ማዕከል የእንሰት አምቾን ስለሰጠን እንዲሁም ለጥናቱ የተባበሩን በሙሉና በሥራና ባላቸዉ ዕዉቀት የረዱን አቶ ያዕቆብ ጎታ፤ አቶ በርገኔ አዴ፤ አቶ ጌታቸዉ ከፍታ፤ አቶ ወርቁ መንትሬ እና አቶ ዘማች ጨሎ ከልብ እናመሰግናለን::

© The authors 2012

Contact: abitew.lag@post.com

# የእንሰት አምቾ አበቃቀል እና የችግኝ ብዜት ጥናት

አብተው ለጅቦ ደልባቶ[1] ላይላ ካርልሰን[1,2] ጣማዶ ጣና[3,4] እና ሚክያስ የሺጥላ[5,6]




የእንሰት ችግኝ አምቾ ከተቀበረ አምስት ወር ወይም አምቾዉ መብቀል ከጀመረ ሁለት ወር ተኩል ጊዜ በኋላ

[1]የስዊድን ግብርና ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ [2]የሊንሾፒንግ ዩኒቨርሲቲ ስዊድን [3]የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ [4]የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ [5]የአረካ ግብርና ምርምር ማዕከል [6]የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ

## 1. መግቢያ

እንሰት በተደጋጋሚ የሚከሰተዉን የአየር ንብረት መዛባት ችግር በመቋቋም ለሰዉ አስተማማኝ የኃይል ሰጭ ምግብ እና ለእንስሳት ደግሞ የመኖ ምንጭ ነዉ። እንሰት በማሳ ላይ ከሚገኙት ሰብሎች ሁሉ የበለጠ ምርታማ በመሆኑ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና አለዉ። የእንሰት ምርት ዉጤቶች ቆጮና ቡላን ለዓመታት ያለብልሽት በባህላዊ ዘዴ ማከማቸት ይቻላል። የጣፋጭ አምቾ እንሰት ደግሞ በማንኛዉም ጊዜ ከጓሮ ተነቅሎና አምቾዉ ተቀቅሎ ይበላል። የእንሰት ምርት ዓመቱን በሙሉ ሊዘጋጅ ይችላል። ስለዚህ እንሰት አስተማማኝና ቋሚ የምግብ ጎተራ ነዉ ለማለት ይቻላል። ባህላዊ መድኃኒትም ነዉ። ቃጫዉና ስታርች ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃነት ይዉላሉ። በእንሰት የተሸፈነ ማሳ ፍግና ብስባሽ ስለማይለየዉ አፈር ለምነቱን አያጣም። በተጨማሪም አፈር በዝናብ ጎርፍና በአዉሎ ነፋስ ተጠርጎ እንዳይሄድ ስለሚከላከል ለዘላቂ ግብርና ልማትና ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለዉ። ተራራማ አምባዎች፣ ሸለቆዎችና ሜዳዎች የእንሰትን ሰፋፊ አረንጓዴ ቅጠሎች ለብሰዉ ሲታዩ፣ አትኩሮ ለተመለከተ እንሰት የዉበትም ምንጭ ነዉ።

## 2. የጥናቱ ዓላማ

ዋናዉ ዓላማ የገበሬዎችን የእንሰት ችግኝ ብዜት ነባራዊ ዕዉቀት (indigenous technical knowledge) በጥናት ለመደገፍ ነዉ። እንዲሁም በዝርያዎች መካከል ያለዉን የአምቾ መብቀል አቅምና የችግኝ ውጤት ልዩነት ለማወቅና የተቀበረ አምቾን ዉሃ ማጠጣት ምን ልዩነት እንደሚያመጣ ለማጥናት ነዉ።

## 3. የጥናቱ ስልት

ጥናቱ የተካሄደዉ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ ነዉ። ከዩኒቨርሲቲዉ ምስረታ በፊት የከብቶች ግጦሽ የነበረ ገላጣ ሜዳ ላይ በጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም 600 ስ.ካ.ሜ ማሳ በእጅ መሳሪያዎች ተቆፍሮ ተዘጋጀ። ዙሪያዉ በሽቦ ከታጠረ በኋላ የጃርት መከላከያ ቦይ ተቆፈረ። የማሳዉ አፈር በሶዶ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪ ተመርምሮ የናይትሮጅን ይዘቱ ዝቅተኛ ነበር። ደረቅ የከብቶች እበትና አፈር በእኩል እጅ በማደባለቅ ፍግ ተዘጋጀ። 63 ተክሎች ከስድስት የእንሰት ዝርያዎች የተመረጡ ሲሆን ዝርያዎቹ በአረካ ግብርና ምርምር ማዕከል ተጠንተዉ፤ በቆጮ ምርት መጠንና በቶሎ ደራሽነት ፀድቀዉ የተለቀቁ ናቸዉ። የሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸዉ፤ በጥሩ ዕድገት ላይ የሚገኙ እናት እንሰት ተክሎች ከተነቀሉ በኋላ፤ ከአምቾዉ በላይ ከሚገኘዉ ግንድ መሰል አካል (pseudostem) አንድ ስንዝር ያህል (18 ሳ.ሜ) ከአምቾዉ ጋር በማስቀረት ተቆረጠ። የአምቾዎቹ አማካይ ክብደት 8 ኪ.ግ ነበር። በስዕል እንደታየዉ ከሙሉ አምቾና ከክፍልፋዮቹ የሙሽራ ቅጠል የሚያወጣዉ ዋና ዓይን (apical bud) በስለታም ቢላዋ ጫፍ በጥንቃቄ ተቦርቡሮና ተቆርጦ ወጥቷል። የተዘጋጁ ጉድጓዶች ጥልቀት 40 እና ስፋት 50 ሳ.ሜ ነዉ። ለስላሳ አፈር 10 ሳ.ሜ ከሥር እየተሞላ አምቾን በማሳረፍ፤በላዩ ላይ አንድ ባልዲ ሙሉ (15 ሊትር) የፍግ ድብልቅ በመጨመር ከዚያም አፈር ተሞላ። አምቾዎቹ ከተነቀሉ በሁለተኛዉ ቀን ጥር 5/2003 ዓ.ም ተቀብረዉ በአፈሩ ላይ ደረቅ ሣር ተጎዘጎዘ። እስከ በልግ ዝናብ ዉሃ እንድጠጡ የተመደቡ አምቾዎች ከሌሎቹ ራቅ ተደርገዉ ተቀብረዉ በየጉድጓዱ በቀን 5 ሊትር ዉሃ ተሰጠ።

## 4. የተገኙ ዉጤቶች

የአምቾ ብቅለት የጀመረዉ በ50 ቀናት ሲሆን በ112 ቀናት ዉስጥ የተቀበሩት 63 አምቾዎች በሙሉ በቅለዋል። ስድስቱም ዝርያዎች (እንዳለ፣ ያንቡለ፣ መሳና፣ ገዋዳ፣ ከልሳ፣ ዘሪታ) ከያንዳንዱ እናት አምቾ በአማካይ ከ28 እስከ 108 ችግኞች ተገኝቷል። ክፍልፋዮች ከሙሉ አምቾ ቀድመዉ ከመብቀላቸዉም በተጨማሪ ብዛት ያለዉን ችግኝ ለማግኘት ተችሏል። በረጅም ደረቅ ወራት የተቀበረ አምቾን ዉሃ ማጠጣት የብቅለት ጊዜን አፋጥኗል፣ ሙሉ አምቾና ክፍልፋዮች በተቀራራቢ ጊዜ በቅለዋል፣ የችግኞቹም ዕድገት ተመሳሳይ ነበር።



**5. ማጠቃለያ** እንሰትን በነባር ማሳ ላይ ለማስፋፋትም ሆነ በአዲስ አካባቢ ለማልማት የችግኝ ብዜት ቀዳሚና ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ተግባር ነዉ። የእንሰት ልማት ቀጣይነት ባለዉና በተጠናከረ ምርምርና ጥናት መደገፍ አለበት።